የቋንቋ መገናኛ ፕሮግራም

የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምብያ የሰብአዊ መብቶች መስሪያ ቤት

# ከቋንቋ ተደራሽነት ዳይሬክተር ሮዛ ካሪሎ የተሰጠ ማሳሰቢያ

አፕሪል ለዲሲ ሰብዓዊ መብቶች ቢሮ በጣም አጣብቂኝ ወር ነበረ። የቋንቋ ተደራሽነት ወርን ማየት እና ማድመቅ ብቻ አይደለም ያደረግነው፣ ነገር ግን ፍትሃዊ የመኖሪያ ቤት ወር፣ የወሲብ ጥቃት ግንዛቤ ማስጨበጫ ወር እና የጸረ-ጎዳና ላይ ጥቃት ሳምንት (አፕሪል 12-18) ጭምር እንጂ።

የቋንቋ ተደራሽነት ቡድን በስራ ላይ ጠንካራ ነበሩ፣ ሁሉም የዲስትሪክቱ ኗሪዎች፣ የኢንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታቸው ምንም ቢሆን፣ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የመንግሥት አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ለማረጋገጥ፣ በ2004 የወጣውን ወሳኝ የቋንቋ ተደራሽነት ሕግ በማስፈጸም። ይህን ለማድረግ፣ ከዲሲ መንግሥታዊ ኤጀንሲዎች እና የቋንቋ ተደራሽነት አስተባባሪዎቻቸው፣ ባለድርሻ አካላትና ከደጋፊዎቻቸው ጋር የጠበቀ ግንኙነት አለን፤ ጉዳይ ከመጣ፣ ግለሰቦች የሚያስፈልጋቸውን አገልግሎቶች መቀበል እንዲችሉ መልስ ለመስጠት ፈጣን ነን።

በቅርቡ FY19 ዓመታዊ የአከባበር ግምገማን በዲስትሪክቱ ውስጥ ለሚገኙ ለሁሉም የመንግሥት ኤጀንሲዎች አውጥተናል እና በሚመጡት ወራት ውስጥ የሆነ ጊዜ የተሻሻለ እትምን እናወጣለን። በተጨማሪም፣ በአሁን ጊዜ OHR ለስብሰባዎቻቸው የቋንቋ አገልግሎቶችን ሲጠቀሙ የትርጉምና የማስተርጎም አገልግሎት ተመላሽ ገንዘብ ሂደትን ለአማካሪ ጎረቤትነት ኮሚሽኖች (ANC) በመላው ከተማ ውስጥ እንዲያስተዳድር የሚያዝ አዲስ ስራ ለቋንቋ ተደራሽነት ፕሮግራም ተሰጥቷል። ለዚህ አዲስ ድንጋጌ አሠራሮችን በመግለጽና ለቋንቋ አገልግሎቶች የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለመጨመር እነሱን ለመደገፍ መርዳት ላይ ከANC ኮሚሽነሮች ጋር መወያየት ላይ ተጠምደናል።

እርስዎ ወይም የሚያውቁት ሰው ኢንግሊዝኛ ችሎታ ስለሌላችሁ ከመንግስት ኤጀንሲ እና/ወይም የገንዘብ ተቋማት ከተመለሱ፣ እባክዎ በ ohr.dc.gov/service/file-discrimination-complaint ቅሬታ ያቅርቡ።

እንኳን ለቋንቋ ተደራሽነት ወር ዲሲ አደረሰዎት!

ከሰላምታ ጋር፣

Rosa Carrillo

የቋንቋ ተደራሽነት ዳይሬክተር